የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 41
ADDIS ABABA 30th June, 2009

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፬/፪ሺ፩ ዓ.ም

ስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለመጠበቅ የተፈረመው ዓለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፯፻፴፰

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 634/2009**

Convention of the Migratory Species of Wild Animals Ratification Proclamation…. Page 4738

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፬/፪ሺ፩

## <u>ስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለመጠበቅ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ዓለም ዓቀፍ ስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. ጁን ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፱ በጀርመን አገር በቦን ከተማ ተፈርሞ ከኖቬምበር ፩ ቀን ፲፱፻፹፫ ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ በመሆኑ፣

ስምምነቱም ስደተኛ የሆኑ የዱር እንስሳት ዝርያ ዎችን በአባል አገራት ትብብር ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚኖረው በመሆኑ፣

ኢትዮጵያ ስምምነቱን መቀበሏ ለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ጠቃሚ መሆኑ ስለታመ ነበት፣

በዚህም የስምምነት አንቀፅ ፲፯ እ.ኤ.አ. ከጁን ፳፪ ቀን ፲፱፻፹ በኋላ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆኑ አገራት ስምምነቱን በማፅደቅ አባል ለመሆን ስለሚችሉ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 634/2009

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION ON MIGRATORY SPECIES OF WILD ANIMALS</u>

**WHEREAS,** the Convention on the Conservation of Migratory Species of Wild Animals was adopted in Bonn, Germany, on 23 June 1979 and came in to force on 1 November 1983;

**WHEREAS,** the said convention is found to have paramount importance in conserving the migratory species of wild animals through cooperation of member states;

**WHEREAS,** it is vital for Ethiopian wildlife conservation effort to be a member of this convention;

WHEREAS, Article XVII of the Convention provides that after the 22 June of 1980 this Convention shall be open for accession by all non-signatory States;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 4th day of June, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “ስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለመጠበቅ የተፈረመው ዓለም አቀፍ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፬/፪ሺ፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

ስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎችን ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. በጁን ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፩ በጀርመን አገር በቦን ከተማ የተፈረመው ዓለም አቀፍ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የማስፈጸም ሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና እንዲሁም ከህብረተሰቡ ጋር በመተባበር ስምምነቱን በሥራ ላይ የማዋልና አፈፃፀሙን የመከታተል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as “Convention of the Migratory Species of Wild Animals Ratification Proclamation No. 634/2009”.

## 2. <u>Ratification of the Convention</u>

The Convention on the Conservation of Migratory Species of Wild Animals signed on the 23rd June of 1979 at Bonn, Germany, is hereby ratified.

## 3. <u>Power of implementation</u>

The Ethiopian Wildlife Conservation Authority is hereby empowered to undertake all acts necessary to the implementation of the agreement in cooperation with concerned Federal and Regional Government Organs and non-governmental organizations as well as communities.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**